ግንቦት ፲፫ ፳፻፪

# ያለነጻነት ፍትሐዊ ምርጫ አይኖርም

በዋሺንግተን ዲሲና አካባቢው የምንገኝ የኢትዮጵያውያን የጋራ ግብረሃይል ባሳለፍነው ወርሃ ሚያዝያ ባወጣነው መግለጫ ፍትሃዊ ምርጫን ለማምጣት ህዝባዊ እምቢተኝነቱ ተቀጣጥሎ ለውጥ እስካልመጣ ድረስ በየ፭ አመቱ ውጤት የሌለው የምርጫ ድራማ ላይ ሃቀኛ ተቃዋሚዎች ከአጃቢነት ራሳቸውን እንዲያገሉ ወገናዊ ጥሪ ማስተላለፋችን ይታወሳል።

ዛሬ ቀጣይና አጭር ማሳሰቢያ ባወጣንበት ቀን የድራማው መጋረጃ ሊከፈት ፳፬ ሰዓታት ይቀሩታል። የዛሬው መልእክታችን ጥሪያችንን ላልሰሙን አጃቢዎች ሳይሆን በምርጫ ሰሞን እንግልቱ ለበዛበት ህዝባችን ነው።

የወያኔ ምርጫ የውሸት መሆኑን ለመገንዘብ ትልቅ እውቀትን የሚጠይቅ ሳይሆን ሰብዓዊ ፍጡር የሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በ ፳፩ የስቃይ አመታት በፍዳው የገበየው ትምህርት ይበቃዋል እንላለን።

የጸረ ህዝቦች እርግጫ የበዛበት ምርጫ ላይ መሳተፍ ለሚናከስ አውሬ ስጋ እንደማቀበል ይቆጠር ይሆን እንጂ፤ የሚገኝ አንዳችም ነገር አለመኖሩን ህዝባችን ያጣዋል ብለንም አንገምትም።

ዛሬ የወያኔ ራስ ምታት ህዝብ በምርጫ ያሸንፈኛል ስልጣኔን ያሰጋዋል ከሚል ሳይሆን የመጪው ፭ አመት ሊቀመንበር ከዓድዋ ወይስ ከመቀሌ ከሽሬ ወይስ ከአክሱም የሚል ነው።

ከዚህ በፊት ካለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በቀር አንሳተፍም ሲሉ የነበሩ እና ሌሎች ሰላማዊ ተቃዋሚዎች እራሳቸው እንኳን አንድ ባልሆኑበት፤ ነጻ ሚዲያ በሌለበት፣ ኮሮጆው ቀዳዳ መሆኑ በሚታወቅበት፣ ቆጣሪው ወያኔ ፣ታዛቢው ወያኔ፣ ባለዱላው ወያኔ፣ ምርጫ ቦርዱ የወያኔ፣ፍርድ ቤቱ የእነሱ ሆኖ እያለ አስቀድመው ተመራርጠው የጨረሱት የምርጫ ውጤት መሆኑ እየታወቀ፤ ታዲያ እንዴት ተደርጎ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ይካሄዳል ተብሎ ወደ ምርጫ ጣቢያ ይኬዳል?

ከላይ የዘረዘርናቸው ባልተደላደሉበት ፍጹም ነጻነት በታጣበት ሰዓት በተባበረ ህዝባዊ አመጽ ወያኔን ለማስወገድ ቆራጥ ህዝባዊ ትግል እንጂ አጃቢነት ለታሪክም ስለማይመች ከዝንጀሮ ቆንጆ ላለመምረጥ ህዝባችን በአንድ ላይ በመቆም ወደ ምርጫ ጣቢያ ባለመሄድ እና ባለመምረጥ ዳግም ተቃውሟችሁን በማሳየት ለአለፉት ፳፩ አመታት በወያኔ የደረሰብንን በደል እንዳይቀጥል የበኩላችሁን በማድረግ ታሪክ እንድትሰሩ በማለት ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ያለ ነጻነት ፍትሃዊ ምርጫ አይኖርም!!!

ጸረ ወያኔ ህዝባዊ እንቢተኝነት ትግል ይፋፋም!!!

ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር!!!

የዋሽንግተን ዲሲ የጋራ ግብረሃይል። dcjointtaskforce@gmail.com